# የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ወይም ሞረሽ እና የዐማራው ጉዳይ?

ሰሞኑን **"የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ወይም ሞረሽ"** ተብሎ ራሱን የሚጠራው ድርጅት በልሳኑ **"የዐማራው ጉዳይ?"** በሚል ርዕስ ያወጣውን መጣጥፍ ላነበብን ይህንን ድርጅት እንመራለን የሚሉን ወገኖች ቆመንለታል የሚሉትን የአማራ ሕዝብ ትግል እንደ ኢሕአፓ ካሉ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚታገሉ ሕብረ-ብሔራዊ ድርጅቶች ጋር የሚያጋጭ ጽሁፍ መበተንን ምን አመጣው ብለን እንድንጠይቅ አድርጎናል። ይህ ድርጅት የተሣከረ የኢሕአፓ ታሪክን በመጣጥፎቹ መነስነሱ ደግሞ የመጀመሪያው አይደለም። ጥያቄው ለምንድር ነው? (የወጣውን ሙሉ መጣጥፍ ከዚህ ትችት ግርጌ ያንብቡት)

በመጀመሪያ በፀረ ወያኔ ትግል ተሰልፈናል የሚሉ ማናቸውም ድርጅቶች የትግላቸው መሠረት ኢትዮጵያዊነት ሲሆን በሀገራችን ኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሠረትና መላ ሕዝቡ ከዳር እስከዳር የሥልጣኑ ባለቤት ሆኖና ሁሉም ዘር፣ ነገድ፣ ብሔር ወይም ብሔረ-ሰብ ተከባብሮ የሕግ የበላይነትን አስፍኖ ሊኖር የሚችልበትን ሁናቴን ማመቻቸት እንደሆነ ሊሠመርበት ይገባል። ከሁሉም በላይ እነዚህ የትግል ድርጅቶችና መሪዎቻቸው በትግሉ ሜዳ ወዳጅና ጠላትን ጠንቅቀው መረዳታቸው የትግል ሀ ሁ እንደሆነ መገንዘብ የግድ ይላቸዋል።

ለምሳሌም ከዚህ በታች በጥቅስ ውስጥ እንደተቀመጠው ዓይነት ኢሕአፓንና ሌሎች ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎችን ጨፍልቆ በአንድ ቁና ለመሥፈር መሞከር ምን የሚሉት እብደት ነው ብለን እንድንጠይቅ አድርጎናል። በዚሕ መጣጥፍ ውስጥ የተደረደረውን የነቀዘ ፍልስፍናና አስተሳሰብ ብዙ ባንተችበትም የውሸት ታሪክና ያልሆነውን ሆነ ብሎ መዘብዘብ ለዛሬው ትግል፣ ወደፊትም ልንመሠርት ለምንታገልለት የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ከሁሉም በላይ ቆመንለታል የሚሉትን የአማራውን ሕዝብ የሚነጥልና ካለአጋር የሚያስቀር የተሳሳተ ቅስቀሳ መሆኑን አለመገንዘባቸው አሳዝኖናል። ስልፋቸው ለመሆኑ ከማን ጋር ነው ብለንም እንድንጠይቅም ሆነናል።

*"የኢትዮጵያዊነት ልዩ መገለጫና የቀጣይነቱ መሠረትና ምሰሶ የሆኑትን ተቋሞች አበጥረው ከለዩ በኋላ፣ ተከታዩ ጥናታቸው እነዚህን ተቋሞች እንዴት ማጥፋት ይቻላል? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ለጥያቄው ሁነኛ መልስ ለማግኘት ጥናታቸውን ቀጠሉ። በጥናታቸውም ኢትዮጵያ አገር እንዳልሆነች፣ የብዙ ነገዶች ስብስብ እንደሆነች፣ እነዚህን ነገዶች ባንድ ላይ አስተሳስሮ የያዘው ዐማራው መሆኑን፣ ዐማራው ከሥልጣን ቢነሳ ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንደማትኖር ግንዛቤ ወሰዱ። ለዚህም ለሥልጣን የቋመጡና የየነገዳቸው አውራ ለመሆን የሚፈልጉ ቀለም ቀመስ ጥራዝ ነጠቅ ማርክሲስት-ሌኒኒስ ነን ባዮችን ከተማሪው መሐል መልምለው አሰለጠኑ፤ አደራጁ፤ አስታጥቀውም ጃዝ አሏቸው። የነዚህ የውጭ ኃይሎች ፍላጎት አስፈጻሚ ሆነው ከተሰለፉት ግለሰቦችና ድርጅቶች መካከል የሚከተሉት ግንባር ቀደምቶቹ ናቸው። በግለሰብ ዋለልኝ መኮንን፣ ጥላሁን ይግዛው፣ ብርሃነ-መስቀል ረዳ፣ ተስፋዬ ደበሣይ፣ እና በተማሪዎች እንቅስቃሴ «አዞ» የሚባለው ቡድን አባሎች የሆኑት ይገኙበታል። ዋለልኝ መኮንን ቅኝ ገዥ ኃይሎች ዐማራው ተነጥሎ እንዲመታ በሮማን ፕሮቻስካ አማካኝነት እኤአ 1935 «ኢትዮጵያ፥የባሩድ በርሚል» በሚል ርዕስ ያሳተመውን የመጽሐፉ አንኳር ጭብጥ «የብሔር ጥያቄ በኢትዮጵያ » በሚል ርዕስ የ1960ዎቹ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ መመሪያ እንዦን በተነ። ይህም ዛሬ በአገሪቱ ላለው የነገድ ፖለቲካና ለሕዝቡ በቋንቋ መከፋፈል ዕንቅላሉን ጥሎ ያለፈ መሆኑ ግልጽ ነው።*

*በድርጅት ደረጃ ፤የቅኝ ገዥዎችን ፍላጎት አስፈጻሚ ሆነው ከቆሙት ጀብሓ፣ ሻዕቢያ፣ ኢሕአፓ፣ ደርግ (ኢሠፓአኮ/ኢሠፓ)፣ ሕወሓት*

*እና አነገ የሚጠቀሱ ናቸው። የሁሉም ድርጅቶች ፕሮግራሞች እነዚህን የኢትዮጵያዊነት ዋና መገለጫ የሆኑ ተቋሞችን በማጥፋት ላይ ያነጣጠረ እንደሆነ ዛሬ አገራችን የምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ አፍ አውጥቶ ይናገራል።"*

ለነገሩ አቶ ተክሌ የሻው የዚህ ድርጅት መሪ የደርግ ኢሠፓ ካድሬና በጊዜውም **"የሠርቶ አደር"** ጋዜጣ አዘጋጅና በኢሠፓ ደርግ ወኪልነትም በተለያዩ ሥፍራዎች ያገለገለ፤ ዛሬ ኢሠፓን በሚኮንን አፉ እንኳን እኔም ኢሠፓ ውስጥ ነበርኩበት ፣ ወገን በቀይ ሽብር ሲጨፈጨፍ የሥርዓቱ አንጋፋ አጫፋሪ ነበርኩ፣ አጥፍቻለሁ ብሉ ሲጸጸት ያልተሰማ ፣ ዛሬ በምን ዓይነት የሞራል ብቃት ለመላው ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረት መሥዋዕት የሆኑ የዚያ ትውልድ ወገኖችን ስም ብቻ በነቂስ አውጥቶ ፣ "የቅኝ ገዥዎችን ፍላጎት አስፈጻሚ ሆነው ከቆሙት…" ብሎ መቀጥቀጡ የሚያስገርም ሲሆን፣ በፀረ-ኢትዮጵያዊነት የተሠለፉ የነፃ አውጪ ነን ባይ ድርጅት መሪዎችና አንቀሳቃሽ ግለሰቦች ስም በጽሑፉ አለመታየቱ ይህንን ድርጅት ማለትም **"የዐማራ ኀልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኀኢአድ) ወይም ሞረሽ"** የአሲምባ ድረ-ገጽ ዝግጅት ክፍል በጥያቄ ውስጥ እንድናስገባ አስገድዶናል። በነገራችን ላይ የአሲምባ ድረ-ገጽ ሀገር ወዳዶች ኢሕአፓን የሚደግፉ ወገኖችንም ጨምሮ የሚያነቡት ቢሆንም ከኢሕአፓ ድርጅት ቁጥጥር ውጪ የሚታተም ነፃ ሚዲያ ስለሆነ በዚህ ድረ-ገጽ ላይ ለሚቀርብ ሁሉ ተጠያቂው የአሲምባ ዝግጅት ክፍል ብቻ መሆኑን እናሳስባለን። ይህንን በየጊዚው ብናስታውቅም እኛን ዝም ለማሰኘት የሚጥሩ ሁሉ እዚህ ድረ-ገጽ ለሚታተም ሁሉ ኢሕአፓን ተጠያቂ ለማድረግ የሚወረወሩት ክሶች በየጊዜው ስለምንመለከት ነው።

**ለማጠቃለል፦**

የአማራው ሕዝብ ተነጥሎ ኢትዮጵያዊነትን በሚጠሉ ወያኔዎችና መሰሎቻቸው የሚደርስበትን ጥቃት ለመከላከል በአማራነት ተጠራትቶ መሰባሰብንና ጩኸቱን ማሰማት የተከበረና ቅዱስ ነው ብለን እናምናለን። ተቃውሞም የለንም። እውነት እንነጋገር ከተባለ ደግሞ ኢሕአፓ ገና ከጧቱ እንደ ዛሬው ፋሽን ከኔ በላይ ለአማራው ድምጽ ለአሣር ነው ከሚሉን በየምሽቱ እንደ እንጉዳይ ከሚፈሉት ስብስቦች በፊት የአማራውን ጥቃት ድምፅ ሆኖ አሰምቷል፣ የጠባብ ብሔረተኞችን ተዋግቷል። መስዋዕትነትን ላገር ለድንበሩ በተራራ ሽንተረሩ ከፍሏል። የአማራ ስብስብ ነው በሚልም በወያኔ ጥቃት ደርሶበት እንደነበርም አንርሳ። ወያኔ፣ ሻብያ፣ የሱዳን መንግሥትና የደርግ ጦር ከበባ አድርገውበት በቋራ ያደረሱበትን ጭፍጨፋ ያስታውሷል። ቀደም ብሎም በአሲምባና በወልቃይት በሻቢያ እገዛም በወያኔዎች ተዘምቶበታል። ዛሬም እንዲሁ። ለአማራው ቆመናል ለሚሉን የምንመክረው ወያኔንና መሠሎቹን ማሸነፍና በኢትዮጵያችን ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር መመሥረት የሚቻለው በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ስንሰባሰብና የማይበገር ኢትዮጵያዊ ኃይል ሆነን የየድርሻችን በመሥራት፣ መተማመንን በጥንቃቄ በመካከላችን በመገንባት፣ ሚዛን መድፋት ስንችል ብቻ ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ በዘርና በጎተ ብቻ አቀርቅረን በመሰባሰብ ዋናውን የኢትዮጵያዊነት ማዕከልና ደጀን ቦርቡረን ሌላውን ጠላት አድርገን እያጥላላን ብቻችንን ተነጥለን እናቸንፋለን ማለት ትልቅ ስህተት ነው።

ይልቅስ ወያኔ ባቀደልን የዘር ቦይ መፍሰስ ብቻውን ለወያኔ ምቶ መመቻቸት ነው ። ወያኔዎችና መሠሎቻቸው የሚፈሩት ትልቁ ኃይል ቢኖር <u>ኢትዮጵያዊነትን ብቻ</u> ነው። ለዚያ ደግሞ ባለፉት 26 ዓመታት ሕዝቡ በኢትዮጵያዊነት መጠቃቀስ የጀመረ የመሰላቸው ጊዜ ሲፍረከረኩና ሲዳናገጡ ማየታችን ትምህርት ሊሰጠን ይገባል። የቅርብ ጊዜውም የአስከኳይ ጊዜ አዋጅ መሠረቱ ይሄ ለመሆኑ ዘወር ብሎ

የቅርብ ጊዜ ታሪክን መፈተሹ ተገቢ ነው። ስለሆነም ነው ወያኔዎችና መሠሎቻቸው ገና በጧቱ ኢሕአፓን ጦር የሰበቁበት። እንደ ኢሕአፓ ያለን ኢትዮጵያዊ ድርጅት ለፖለቲካ ፍጆታ ብሎ ከሕዝብ ለመነጠል መሞከር ወያኔ በቆፈረልን ቦይ ኮለል ብሎ መፍሰስ ብቻ ሳይሆን ጸረ ኢትዮጵያ አተላውንም መሸከም ነው ብለን እንፈርጀዋለን።

ስለሆነም በ“**የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ወይም ሞረሽ”** ጥላ ሥር ለተሰባሰቡ ሁሉ እንዲያው ክሊሼ ባይሆንብን የምናሳስበው ኢሕአፓን ለቀቅ ወያኔንና መሠሎቹን ጠበቅ አድርጉ ነው። በነገራችን ላይ ሀገራችንን ለጥፋት ያበቃው የውጪውን ፍልስፍና መማር ወይም ኮሙኒስት ግራ ዘመም አስተሳሰብ ወይም ደግሞ የብሔር ብሔረ-ሰብ ነፃነት ብሎ የዴሞክራሲ ጥያቄ ማንሳት ሳይሆን ጸረ-ዴሞክራሲ ግለሰቦች ለሕዝቡ እኔ ብቻ አውቅለታለሁ የሚሉ እብዶች ያመጡብን መዓት ነው። ሕዝቡን የሥልጣኑ ባለቤት ማድረግ ማለት ደግሞ ግለሰቦችን ወይም ፓርቲዎችን የመንግሥት ሥልጣን ማስጨበት ማለት እንዳልሆነ ማወቅ ትልቅ ችሎታ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ያጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል!

የአሲምባ ድረ-ገጽ ዝግጅት ክፍል

ማሳሰቢያ ለአንባቢያን፥

ይህች ልዩ አምድ በአሁኗ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን ሥርዓት አንኮታኩቶ ለመጣል ከመቼዎም የበለጠ የተነሳሳበትና ትግሉንም በሕብረ-ብሔራዊ መልክ መቅረጽን የተረዳበት ለመሆኑ በቅርቡ በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄዱት ሰላማዊ ሰልፎችና ሕዝባዊ አመጾች ያሳያሉ። ይህም የትግል አቅጣጫ ወያኔንና ደጋፊዎቹን፣ ተለጣፊዎቹን አስደንግጧል። የሕዝብ አመጻ እየገፋ በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ የኃይል ሚዛን ለውጥ ስለሚኖር ያንን ለመገደብ ወይም ጠልፎ ለራስ ለማድረግ በወያኔም በኩል በሁሉም የሕዝብን ድምፅ እያሰማ የሚመጣ ስብስብና ቡድን እንደ አሸን የሚፈላበት ወቅት ስለሆነ የአሲምባ አንባቢያን ግንዛቤን እንዲያገኙ አለፍ አለፍ ብለን ከድህረ-ገፆች አካባቢና ከሌሎችም ያገኘናቸውን አጠር ካለ አስተያየት ጋር የምናቀርብበት አምድ ይሆናል።

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ)
Amara Survival for Ethiopia’s Unity Organization (ASEUO)

**ቅጽ 1 ፤ ቁጥር 7** **ቀን፡- ማክሰኞ ነሐሴ 23 ቀን 2009 ዓ.ም.**

# የዐማራው ጉዳይ?

ዐማራው በኢትዮጵያ አንድነት በጽኑ የሚያምን ሕዝብ ነው። ለነፃነት ቀናዒ ነው። ፍትሕ አክባሪና ፈላጊ ነው። ጀግንነት ከርኅራኄ እና ከየዋሕነት ጋር ለንቅጦ የያዘ ነው። ይህ አቋሙና እምነቱም በተለያዩ ጊዜአቶች ተነስተው ለነበሩ ተስፋፊዎችና ቅኝ ገዥዎች ፍላጎት የሚመች አልሆነም። በመሆኑም በተደጋጋሚ ሊወሩትና ቅኝ ተገዥ ሊያደርጉት የሞከሩትን ድባቅ በመምታት ነፃነቱን፣ ክብሩንና ማንነቱን አስጠብቆ የዘለቀ የብቸኛ ነፃ አፍሪካዊ አገር ባለቤት ለመሆን የበቃ ነው። ይህ የፀና እምነቱና አቋሙ በቅኝ ገዥዎች ጥርስ እንዲገባ አደረገው።

ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያ ጂኦ-ፖለቲካ አቀማመጥ፣ የቀይ ባሕር ምዕራባዊ ዳርቻ ባለቤት መሆን፣ አገሪቱ የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች ባለቤት መሆን የየዘመኑን ኃያላን ትኩረት እንድትስብ አድርጓታል። ይህም የቅርብም የሩቅም ጠላቶቿ እንዳይተኙላት የስበት ኃይል ሆኖ ማገልገሉ አልቀረም። ይህም ተስፋፊዎችና ቅኝ ገዥዎች ኢትዮጵያን በፈለጉት መልኩ እጃቸው ለማድረግ የቀጥታ ወረራ በተደጋጋሚ እንዲያደርጉ ግፊት ሰጣቸው። ወረራው ግን ጀግኖቹ አባቶቻችን በድኖዋ፣ በእንትጮ፣ በጉራ፣ በጉነደት፣ በሣርውኃ፣ በአምባላጌ፣ መቀሌ፣ ዐድዋ፣ ማይጨው፣ እንዳባጉና፣ ተንቤን፣ አጋዴን ወዘተ ባስመዘገቡት የነፃነትና የማንነት ድል ኢትዮጵያ «የነፃነት ምሽግ» የተሰኘ ስም ባለቤት እንድትሆን አድርጓታል።

ጀግኖች አባቶቻችን በከፈሉት የሕይዎት ዋጋ ፤ኢትዮጵያ የጥቁሩ ዓለም ሕዝብ በነፃነት፣ በጀግንነት፣ በአይበገሬነት ምሳሌ እንድትሆን አስችሏታል። የማንነትና የነፃነት ድሎቹ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን የኩራትና የአይበገሬነት ስሜትን ያጎናጸፈንን ያህል፤ ድል ሆነው የተመለሱትን ተስፋፊዎችና ቅኝ ገዥ ኃይሎች ደግሞ፣ እንዴት ተሸነፍን? ለምን ተሸነፍን? እኛ ሥልጡንና የዘመናዊ አውዳሚ የጦር መሣሪያዎች ባለሌት ሆነን እያለ፣ እንዴት በኋላቀርና በገበሬ የከተት ሠራዊት እንሸነፋለን? የሚል ቁጭት፣ ብስጭትና የመጠቃት ስሜት እንዲቋጥሩ አድርጓቸዋል። ይህን ቁጭታቸውንና ሽንፈታቸውን ለመበቀል ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንቅልፍ አጥተው ለዘመናት አስበዋል። ሀሳቦችን አውጥተው አውርደዋል። በዚህ ጥረታቸውም ለሽንፈታችንና ለእኛ ዓላማ ፀር-ሆኖ የቆመው የትኛው ነገድ ነው? እርሱንስ ለማጥፋት ምን ማድረግ አለብን? ብለው እንዲጠይቁና መልሱንም በጥናት ማረጋገጥ አለብን ከሚል መደምደሚያ ላይ ደረሱ።

ባደረጉት ሠፊ ጥናትም፣ ሌሎች የአፍሪና የእስያ አገሮችን በመናኛ ሥጦታዎችና በወንጌል ሰባኪዎች ስም እጅ ስናደርግ፣ ኢትዮጵያን ከሥጦታና ከወንጌል ስብከት አልፎ፣ በተጠናከረ ወታደራዊ ኃይል የፍላጎታችን ተገዥ ማድረግ ያልቻልነው ከሌሎች አገሮች በተለየ ሁኔታ ምን ስላላት ነው?ብለው ለጠየቁት ጥያቄና ላደረጉት የመልስ ፍለጋ ፤ሦስት ጠናካራና ዘመን ጠገብ ተቋሞች ስላሏት ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ደረሱ። እነዚህ ተቋሞችም የሥልጣን ምንጭ እና የአንድነት ምልክት የሆነ ዘውዳዊ ሥርዓት፣ የዘውዱ ርዕዮተ-ዓለማዊ መሠረትና የሕዝቡ ሃይማኖት የሆነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት፣ እንዲሁም፣ በዘውዳዊ ሥርዓቱ በጥብቅ የሚያምን፣ የአንድነት አፍቃሪ፣ ጀግናና ተዋጊ፣ ማንነቱን በኢትዮጵያዊነት የሚገልጽ ዐማራ የተሰኘ ነገድ መሆናቸውን አረጋገጡ።

የኢትዮጵያዊነት ልዩ መገለጫና የቀጣይነቱ መሠረትና ምሰሶ የሆኑትን ተቋሞች አበጥረው ከለዩ በኋላ፣ ተከታዩ ጥናታቸው እነዚህን ተቋሞች እንዴት ማጥፋት ይቻላል? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ለጥያቄው ሁነኛ መልስ ለማግኘት ጥናታቸውን ቀጠሉ። በጥናታቸውም ኢትዮጵያ አገር እንዳልሆነች፣ የብዙ ነገዶች ስብሰብ እንደሆነች፣ እነዚህን ነገዶች ባንድ ላይ አስተሳስሮ የያዘው ዐማራው መሆኑን፣ ዐማራው ከሥልጣን ቢነሳ ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንደማትኖር ግንዛቤ ወሰዱ። ለዚህም ለሥልጣን የቋመጡና የየነገዳቸው አውራ ለመሆን የሚፈልጉ ቀለም ቀመስ ጥራዝ ነጠቅ ማርክሲስት-ሌኒኒስ ነን ባዮችን ከተማሪው መሐል መልምለው አሰለጠኑ፤ አደራጁ፤ አስታጥቀውም ጃዝ አሏቸው። የነዚህ የውጭ ኃይሎች ፍላጎት አስፈጻሚ ሆነው ከተሰለፉት ግለሰቦችና ድርጅቶች መካከል የሚከተሉት ግንባር ቀደምቶቹ ናቸው። በግለሰብ ዋለልኝ መኮንን፣ ጥላሁን ይግዛው፣ ብርሃነ-መስቀል ረዳ፣ ተስፋዬ ደበሣይ፣ እና በተማሪዎች እንቅስቃሴ «አዞ» የሚባለው ቡድን አባሎች የሆኑት ይገኙበታል። ዋለልኝ መኮንን ቅኝ ገዥ ኃይሎች ዐማራው ተነጥሎ እንዲመታ በሮማን ፕሮቻስካ አማካኝነት እኤአ 1935 «ኢትዮጵያ፥የባሩድ በርሚል» በሚል ርዕስ ያሳተመውን የመጽሐፉ አንኳር ጭብጥ «የብሔር ጥያቄ በኢትዮጵያ » በሚል ርዕስ የ1960ዎቹ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ መመሪያ እንሆን በተነ። ይህም ዛሬ በአገሪቱ ላለው የነገድ ፖለቲካና ለሕዝቡ በቋንቋ መከፋፈል ዕንቅላሉን ጥሎ ያለፈ መሆኑ ግልጽ ነው።

በድርጅት ደረጃ ፣የቅኝ ገዥዎችን ፍላጎት አስፈጻሚ ሆነው ከቆሙት ጀብሓ፣ ሻዕቢያ፣ ኢሕአፓ፣ ደርግ (ኢሠፓአኮ/ኢሠፓ)፣ ሕወሓት እና ኦነግ የሚጠቀሱ ናቸው። የሁሉም ድርጅቶች ፕሮግራሞች እነዚህን የኢትዮጵያዊነት ዋና መገለጫ የሆኑ ተቋሞችን በማጥፋት ላይ ያነጣጠረ እንደሆነ ዛሬ አገራችን የምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ አፍ አውጥቶ ይናገራል። ዘውዳዊ ሥርዓቱን በተማሪ ጫጫታ ደርግ አፈረሰው። ከዘውዳዊ ሥርዓቱ ጋር ተያይዞ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የነባራትን «ሢሶ ያንጋሽ፣ ሢሶ የቀዳሽ» መብቷን ቀምቶ፣ በመንግሥት ውስጥ ትጫዎት የነበረውን ሚናዋን ከማሳጣት አልፎ፣ ሕዝቡ ፀረ-ሃይማኖት አቋም እንዲይዝ የሚችለውን ሁሉ አደረገ። በውጭ ኃይሎች በተገዙ የተማሪዎች እንቅስቃሴ መሪዎች ለሚገፉው «የመሬት ላራሹ» ጥያቄና ለፍትሕና ዕኩልነትን መነሻ አድርገው ለሚቀነቀኑ የብሔረሰብ መብት ጥያቄዎች፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ተገቢ መፍትሔ መስጠት አለመቻል፣ በወሎ የተከሰተው ድርቅ ያስከተለው ዕልቂት፣ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ያስነሳው ሕዝባዊ ቁጣ፣ የኑሮ መወደድ በወታደሩ የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ያሳደረው ቁጣ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ሁኔታ ያስከተለው ሕዝባ አመጽ፣ ሕዝቡ የኋላውን ሳያይ፣ ምን ሊመጣ እንደሚችል በቂ ግንዛቤ ሳይኖረው ፣በሥርዓቱ ላይ ያሳደረው ግፊት ለዘውዳዊ ሥርዓቱ መውደቅና ለደርግ ሥልጣን መቆጣጠር ምቹ መንገድ የፈጠረለት እንደሆነ ይታወቃል። ደርግም የሥልጣን መቆያ፣ የኃይል መደላድል ይሆነኛል ብሎ የተከተለውን ስልት፣ ከኢትዮጵያ ታሪክ፣ ለረጅም ዘመን ትከተለው ከነበረውና፣ ለኅልውናዋ መጠበቅ ዋልታና ማገር የሆኑት ተቋሞች የትኞቹ እንደሆኑ ሳይለይ፣በግብታዊነት በወሰደው እርምጃ ሁለቱን ጥንታዊ ተቋሞች ማለትም ዘውዳዊ ሥርዓቱንና የኢትዮጵያን ኦርቶዶክሶ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአንድ አዋጅ አፈረሳቸው። ይህ ኢትዮጵያን ለመበታተን ሌት ተቀን ሲጥሩ ለነበሩ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ታላቅ የምሥራች ሆነላቸው። «እስበሱ ሥጋን በኩበት ጠበሱ» የሚሉት የአባቶቻችን ቃል ሕያው ሆኖ፣ በገንዘብ፣ በወንጌል ማስፋፋት እና በታጠቀ ጦር ሠራዊት እጅ ለማድረግ ያልቻሏትን ኢትዮጵያን፣ ዕርስ በርሳችን በማናከስ ወደ ግባቸው እያመሩ ይገኛሉ።

ደርግ በመደብ ትግል እና የሶሻሊስት ርዕዮተ-ዓለም በማስፋፋት ስም ከፍተኛ የሆነ ሕዝብ እንዲገደል፣ እንዲሰደድ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥቅምና መብቱን እንዲነጠቅ ያደረገው የዐማራውን ነገድ እንደሆነ ይታወቃል። በሌላ በኩል ደርግን እንዋጋለን፣ የየነገዳችን መሪ እንሆናለን፣ ከኢትዮጵያ እንገነጠላለን ብለው ጫካ የገቡ ቡድኖችም በአውራ ጠላትነት ፈርጀው የጥፋት እጃቸውን ያነሱት በዐማራው ላይ ነው። ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ዘውዳዊ ሥርዓቱ፣ ኦርቶዶክስ ሃይማኖቱና የዐማራው ነገድ ተያያዥና ተደጋጋፊዎች ነበሩ። ይህ ተደጋጋፊነትና ተባባሪነት እንዳይኖር ለያይቶ መምታት ያስፈልጋቸው ነበርና፣ ዘውዳዊ ሥርዓቱና ሃይማኖቱ ባንድቀን አዋጅ እንዲፈርሱ ሲደረግ፣ ዐማራው ብቻውን ቀረ። የሚገርመው ዐማራው ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ልጆቹ ምን ሊመጣና ሊከተል እንደሚችል ለማሰብና ከመጭ አደጋዎች እንዴት መከላከል እንደሚቻል ዘዴ አልዘየዱም። ዐማራው በዘር ተልይቶ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል እየተፈጸመበት እያዩና እየሰሙም ለምን ያሉት እግጅ ጥቂቶች ናቸው። ይህም በመሆኑ በዛሬዋ ኢትዮጵያ ዐማራው የመኖርና ተዘዋውሮ የመሥራት መብቱን ተነፍጎ፣ በተገኘበት እየታደነ በመገደል ላይ ነው። ባለፉት 26 ዓመታት የትግሬ-ወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ከአምስት ሚሊዮን በላይ ዐማራ ከምድር ገጽ እንዲጠፋ ተደርጓል። ይህ አልበቃ ብሎ የመዋለድ መብቱን በሕዝብ ዕድገት መቆጣጠሪያ ስም መካንና ታማሚ እያደረጉት ነው።

ከሁሉም በላይ ዐማራው በብዛት የሚኖርባቸውን ጠቅላይ ግዛቶች ሕዝብ ፣ከዐማራው ውጭ ነኝ ወይም አገው ነን፣ ኦሮሞ ነን፤ እና ቅማንት ነን የሚሉትን ፣ከዐማራው በመነጠል የየራሳቸው አስተዳደር እንዲመሠርቱ አድርገዋል። ይህ ድርጊት ለነገዶችና ጎሳዎች ዕኩልነት ታስቦ ከሆነ፣ ሥራው መጀመር የነበረበት ትግራይ ውስጥ በትግሬዎች ለተጨቆኑት ኩናማዎች፣ ሣሆዎች፣ ኢሮቶች፣ አገዎች፣ አፋሮችና ኦሮሞች መሆን ነበረበት። ወያኔ የትግራይን ግዛት እስከ ቤንሻጉል ለማስፋት ባለው የቆየ የመሥፋፋት ዓላማ፣ ሰሜን ጎንደርን የግዛቱ አካል ለማድረግ ላቀደው ዕቅድ ተፈጻሚነት እንቅፋት ከጎንደር ሕዝብ እንዳይገጥመው በማሰብ ቀድሞ ቅማንቶቹን አደራጅቶ በፀረ-ዐማራው ግንባር ተሳታፊዎች እንዲሆኑ እያደረገ ነው። በጎንደር ዐማራና በቅማንት ሕዝብ መካከል ምንም ዓይነት ቅራኔና ልዩነት እንዳልነበር ማንም ያውቀዋል። ሆኖም የፀረ-ኢትዮጵያ ፍላጎት አስፈጻሚ በሆነው የትግሬ ወያኔ ጥቅም የተገዙ ጥቂት የቅማንት ተወላጆች ጽሕፈት ቤታቸውን መቀሌ እና አዲስ አበባ ላይ አድርገው ወያኔ በሚሰጣቸው ሁለንተናዊ ድጋፍ የጎንደርን ዐማራ አርዶ ጨርሶ የመሬቱ ባለቤት ለመሆን እየጣሩ እንደሚገኙ ይታወቃል። ይህ በቅማንትና በዐማራ ሕዝቦች መካከል ሆን ተብሎ የተፈጠረ ችግር የሚጠቅም ከሆነ የሚጠቅመው ወያኔንና ግብረ አበሮቹን እንጂ፣ የቅማንትን ሕዝብ ሊሆን ከቶ አይችልም። በመሆኑም በዚህ በወያኔ ጀሌነት ሁለቱን ነገዶች ዓይንና ናጫ ለማድረግ የተሰለፋችሁ የቅማንት ወንድም እህቶቻችን ከዚህ ድርጊታችሁ እንድትታቀቡና ወደ ጥንት ጧቱ የአንድነት ስሜት እንድትገቡ ጥሪያችን እናቀርብላችኋለን። ይህን ጥሪአችን በማይቀበሉና ወያኔ የጫናቸውን ተሸከመው የሚጓዙ ጌኛዎችን የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ትምህርት ሰጭና ማስጠንቀቂያ የሆነ ርምጃ ሊወስድ የሚገደድ መሆኑን ከወዲሁ ለማሳወቅ እንወዳለን።

የግፍ ዓይነት ተቀባይና ዘርህ እንዲጠፋ የተፈረደብህ የዐማራ ወጣት ነገ ሳትል ፣ዛሬ የሕዝባዊ እንቢተኝነቱን እንቅስቃሴ እንድትቀላቀል ጥሪያችን እናቀርብልሃለን። የወያኔ ጀሌ ሆኖ በወገኖቹ ላይ ጥፋት የፈጸመ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በቀር የትም ለማምለጥ እንደማይችል አውቆ፣ ከዐማራ ወገኑ ጎኑ እንዲቆም እንመክራለን። በብአዴን ውስጥ ያላችሁ የዐማራ ልጆች «ከዘላለም ባርነት፣ የአንድን ቀን ነፃነት» በመምረጥ ከወገናችሁ ጎን እንድትቆሙ ራሳችሁ ለራሳችሁ ቃል እንድትገቡ እናሳስባለን። «ሊነጋ ሲል ይጨልማል» እና፣ በዐማራው ላይ ጨልሞ የነበረው የወያኔ የ26 ዓመታት ጥቁር ጨለማ በዐማራው ልጆች ተጋድሎ ብርሃን ማሳየት ጀምሯል። ይህ በኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ ጥይት አብሪነት፣ በጎቤ መልኬ መስዋዕትነት የተጀመረው የዐማራ ተጋድሎ እንቅስቃሴ ወያኔን ወደ መቃብሩ ሳይከት አይጠፋም። ብርሃኑ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን የሚዳረስና የዘላለም እንዲሆን፣ኢትዮጵያውያን በዐማራው ትግል ዙሪያ የምትችሉትን ሁሉ እንድታደርጉ ጥሪያችን እናቀርባለን። ድል የመስዋዕትነት ፍሬ ነውና፣ ለድሉ በምንችለው መስዋዕት ለመክፈል ዝግጁ እንሁን!

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!